# አገር ሠሪ፣ አገር አልባ ሕዝብ!

## ዐማራው በትግሬ ወያኔ-ኦነግ አገር የለሽ ተደርጓል!

ዐማራ እግሩን ለጠጠር፣ ደረቱን ለጦር ሰጥቶ ኢትዮጵያን እንደ አገር ከሠሯት ነገድና ጎሣዎች መካከል አንዱና ግንባር ቀደሙ መሆኑን የአገሪቱ የረጅም የመንግሥትነትና አገራዊነት ታሪክ ያስረዳል። ዐማራው ቋንቋን ከፊደል፣ ሃይማኖትን ከሥርዓት፣ ሕግን ከባህል፣ አጣጥሞና አዋሕዶ ለኢትዮጵያውያን የወል ማጠቀሚያነት ያበረከተ ሕዝብ ነው። ጀግናና ኩሩም ነው። የዛሬውን አያድርገውና፣ መብቱ ሲነካበት የማይወድ፣ ለማንነቱና ለነፃነቱ ቀናዒ ሕዝብ የነበረ ነው። እነዚህ ማለፊያዎቹ መሆናቸውን የድሆኖ፣ የእንትጮ፣ የሣር ውኃ፣ የመተማ፣ የዐድዋ፣ የአምባላጌ፣ የወልወል፣ የቆራሄ፣ የመቀሌ፣ የማይጨው ወዘተ ጦር ሜዳዎችና የተገኙት ድሎች ሕያው ምስክሮች ናቸው።

ይሁንና ዛሬ የትናንት አገር ሠሪው አገር አልባ እንዲሆን ተደርጓል። በተገኘበት ማንም ያሻውንና የፈለገውን ግፍ የሚፈጽምበት እና የግፍ ዓይነቶች ማለማመጃ ሆኗል። ከ1972 ዓም ጀምሮ፣ ወልቃይ፣ ጠገዴ፣ ጠለምት፣ ራያ እና ቆቦ፣ ወረዳና አውራጃዎች ነዋሪ ዐማራዎች ፣ እንዲሁም ከ1983 ዓም ጀምሮ ሐረርጌ፣ ወለጋ፣ ኢሉባቡር፣ ከፋ፣ ጎጃም(መተከል) ወዘተ ክፍለ-ሀገሮች ነዋሪ በሆኑ ዐሞሮች ላይ፣ የተፈጸመውና እየተፈጸመ ያለው ጅምላ ግድያ፣ እሥራት፣ ግርፋት፣ ሚፈናቀል፣ ማዋከብ፣ ዘር ማጥፋትና ዘር ማጽዳት መሠረት ያደረጉት፣ «የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት» ከተባለው የወያኔ-ኦነግ የጥፋት ሰነድ ነው። ይህ ደግሞ የተዘጋጀው የዐማራ ጥላቻን ገንብቶ ባደገው ማለስ ዜናዊና እርሱ በሚራው የኦነግ ቡድን ነው። አስፈጻሚዎቹም የትግሬ-ወያኔ በልኩ ብቻ ሳይሆን፣ እንዲህ ሊያስቡ ይችላሉ ብለው በሚጩ ቅ የጌቶቻቸውን ዕኩይ ዓላማዎች በከፋ እና በባሰ ሚልኩ ለማስፈጸም ባምሳላቸው ኮትኩተው ባሳደጓቸው ባንዳዎች ነው።

አንባቢ ልብ ብሎ እንዲከታተል የምንጠይቀው፣ ይህ ሕገ-መንግሥት ፣ዐማራውን ከሌሎች ነጥሎ እንደጢቃ፣ እንዲሳደድ፣ እንዲፈናቀል፣ እንዲወገዝ፣ በጥቅሉ የዘር ጥቃት እንዲፈጸምበት የተቀመረ መሆኑን ነው። ዐማራውን ለይቶ ለማጥቃጥና በአዝግሞት ለማጥፋት ያለመ ዓላማን በማየዙ፣ ሕገ-መንግሥቱ ለዜጎች ዕውቅናን ከማስጠት ይልቅ፣ ዕውቅናን ለዘር የሰጠ ነው። በመሆኑም ሕገ-መንግሥቱ ሆን ተብሎ፣ በጅምላ የዐማራን ሕዝብ እንዲያገል ተደረገ። ሕዝብ ሳይመክርበትና ሳያውቀው ተግባራዊ ተደረገ። ሕገ-መንግሥቱ በግለሰቦች መብትና ጥቅም ላይ እንዲመሠረት ቢደረግ ኖሮ፣ የዐማራው መብትና ጥቅም የሚከበር እንደሚሆን ማለስ ስለሚረዳ፣ ብቸኛውና ሥልታዊው የዐማራው ማጥቂያና ማጥፊያ መንገድ ሕገ-መንግሥታዊ መብት ማስከበሪያው መንገድ ቡድናዊ ወይም ብሔረሰባዊ እንዲሆን አደረገ። የአገሪቱን ሕገ-መንግሥት ዓለም የተቀበለውን የግለሰብ ነፃነትንና የዜግነት ለዕልናን ደፍቆ የአገራዊ ባለቤትነትን ለብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሰጡ። በተዋረድ የፀረ ዐማራው ሕገ-መንግሥት የክልል መንግሥታት ተብዬዎች ዐማራውን በዘር ለመጥረግ የሚያስችላቸው የራሳቸው ባለሕገ-መንግስት እንዲሆኑ አደረገ። አንባቢ ከታች ያለውን ማስረጃ በገሀድ እንደሚያየው ከዐማራው ክልል ተብዬ ውጪ ያሉት ክልሎች፣ የክልላቸው ሀብትና ሥልጣንን ሙሉ የባለቤትነት መብት ሲሰጥ፣ በግዛታቸው ውስጥ ለሚኖሩት በቁጥርም ከሌሎቹ የሚገሰውን ዐማራውን ነጥሎ በማውጣት እውቅና እንዲነፍገው ተደርጎ ተቀምጧል።

በተቃራኒው፣ ለዐማራው ክልል ተብሎ በተሰየመው ሜዴት ላይ፣ ለሌሎቹ የተሰጠው የባለቤትነት ሥልጣን ተነፍጎታል። ወይም እሱን፣ ዐማራው የሥልጣን ባለቤትነት እንደሆነ አይገልጽም። ይልቁንም ግዛቱን በትግሬ-ወያኔ ቡድን፣ በኦነግና በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብለው በፈጠሩት ግዛት መሀል ተቀራምተውታል። ለሱዳን የወዳጅነት መግዢያ አድርገውታል። ክልሉን በጎሳ ልዩ ዞኖች ሸንሽነውታል። በዐማራው ስም በተከለለው ክልልም የሜዴትና የግዛት ባለቤትነት አልተሰጠውም። ባገሪቱ ባሉ ታላላቅ ከተሞች የዐማራው ሕዝብ ቁጥር የሞገሰ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም፣ ባንዳቸውም ውስጥ ውክልና የለውም። በአዲስ አበባ ውስጥ የዐማራ ሕዝብ ቁጥር ከ50% በላይ መሆኑ የታወቀ ነው። ይሁንና በከተማዋ አስተዳደር መብት የለውም ። በዚህም የተነሳ፣ በኦሕዴድ በሚሾሙ ከንቲባ ተብየዎች የከተማዋን የሕዝብ

አሠፋፈርና ሥብጥል ትግሬ ጠቀምለማድረግ፣ በተጠና እና ስልታዊ በሆነ መንገድ ዐማራውን በሚፈናቀል ቤቱን በግሬደር በማፍረስ ለዘመናት ከኖረበት አካባቢ በማስወጣት ማጤ ሠፋሪና ተሸማቃቂ አድርገውታል። ዓላማው ቀስበቀስ ዐማራውን በማስወጣት ሌሎች እንዲሠፍሩበት በማድረግ ነባሩን የሕዝብ ትስስር ለማጣጣስና ከተማዋን ያንድ ብቸኛ ነገድ አንጡራ ሀብት ባለቤት ለማድረግ የተያዘ ሤራ መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። ልዩ ጥቅምበሚል በሕግ ሽፋን ከሚደረግ የስምማዝወርና የሕዝብ ነቀላና ተከላ፣ የዘር ማጥፋት ፕሮግራም ጋር በትይዩ ተያይዞ በመካሄድ ላይ ያለ መሞሪያ ነው። መብትና ሥልጣን የተሰጠው፣ እንደ አገሪቱ ሕገ-መንግሥት ለብሔር/ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ነውበሚል የዐማራ ጥፋት በስፋትና በእቅድ እየተካሄደ መሆኑን ለሚረዳት ስለአገራዊ የሥልጣን ባለቤትነት ሕገ-መንግሥቶቹ የሚደነግጉትን በዝርዝር መመልከት ተገቢ ይሆናል።

## 1 የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት፡-

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሪያዊት ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 ስለአገራዊ የሥልጣን ባለቤትንነት እንዲህ ይላል። **«የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች፤ ሕዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው» ይላል።**

የዚህ ሕግ ማሻና መንደርደሪያ አንኳር ሀሳቡ የሚሞጨው በሕገ-መንሥቱ መግቢያ ላይ፣ **«እኛ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች---»** በማለት ከሚጀምረው የዓላማው ቀዳሚ ሀሳብ ነው። ይህ ለሕገ-መንግሥቱ ቀዳሚና ዋና ዓላማተደርጎ የተያዘ ሀሳብ፣ ዕውቅና የሚሰጠው **«ብሔር/ ብሔረሰብ እና ሕዝቦች»** ለሚላቸው፣ ቡድኖች ነው። ሕገ-መንግሥት ተብየው ለአገሪቱ ዜጎች የዜግነት መብትን ነፍጓል። የአገሪቱ ባለቤትነት የተሰጣቸው ቡድኖች፣ እነማን እንደሆኑ፣ ቋንቋን ብቻ ብቸኛ ማስፈርት ባደረገ የልዩነት አሀድ ላይ ላሉ ቡድኖች የተሰጠ ዕውቅና ነው። በዚህ ሕገ-መንግሥት የዲሞካራሲና የሰብአዊ መብት ማጠበቅ ዋልታና መሠረት ለሆነው፣ የግለስብ መብትና ነፃነት ዕውቅና አይሰጥም፡ ይህምበመሆኑ፣ በዚህ ሕገ-መንግሥት የተናጠል ዜጎች መብትና ነፃነት ዕውቅና የተሰጠው አይደለም፡ ምክንያቱም ለግለሰቦች መብት ከተሰጠ «የዓይኑ ቀለም አላማራኝም» ብሎ የፈለጉትን ለማድረግ አያስችልም፡ ይህን ማድረግ ካልተቻለ ደግሞ አውራ ጠላቴ ብሎ የፈረጀውን እና እንዲጠፋ የፈለገውን ዐማራ ለማጥፋት ከፍተኛ ማሰናክል እንደሚሆንበት ወያኔ ተረድቷል። ዋናውም የሕገ መንግስቱ ማሻ ዓላማው ዐማራውን ነጥሎ ለማጥፋ በመሆኑ በዘር ላይ የተዋቀረ ሕገ-መንግሥት ዋና ማሳሪያውመሆኑን በሚገባ የተረዳ ጠላታችን ነው።

ይህም በመሆኑ፣ በዓለም የታወቀና ተቀባይነትን ያገኘ የአንድ መንግሥት ማሻ የሆነው ዜጋ የኀልውናምሆነ የአገር ባለቤትነት መብት እንዳይኖረውተደርጓል። ግለሰቦች አገሬ ለማለት መብት የላቸውም፡ ምክንያቱም ሕገ-መንግሥቱ ዕውቅናን ነስቷቸዋልና። አያውቃቸውም፡ ዜጎቼ አይላቸውም፡ ይህምበመሆኑ የግለሰቦች መብትና ነፃነት ላለፉት ዓመታት ብቻ ሳይሆን፣ ለሚጪዎቹም፡ ይህን ሕገ-መንግሥት በመሠረታዊ የለውጥ እርምጃ እስካልተሻረ ድረስ፤ የግለሰቦች መብትና ነፃነት የሚገጥና የማታፈን ጉዳይ በ «ሕጋዊነት» ስምይቀጥላል። በተለይምለዐማራ ሕዝብ የሚጠብቀው አጠቃላይ ጥፋት ነው።

ከፍ ሲል ለማሳየት እንደተሞከረው፣ በዚህ የትግሬ-ወያኔ ሕገ-መንግሥት ለዜጎች ዕውቅና ያልሰጠ በመሆኑ፣ ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች፣ በግለሰብ ደረጃ አገሬ የሚሉት ነገር የላቸውም፡ ከዐማራው በስተቀር ሌሎች ነገዶች፣ አገር የሚኖራቸውራሳቸውን ባንዱ ወይምበሌላውነገድ/ ወይምጎሣ፣ እንደ ወያኔውአጠራር የብሔር/ ብሔረሰብ/ ሕዝቦች አባል ሲያደርጉ ብቻ ነው። ይህምየራሱ የሆነ ችግሮች አሉት። ከዐማራውውጪያሉት ነገድና ጎሳዎች(ብሔር/ ብሔረሰቦች/ ሕዝቦች) ከኢትዮጵያ ውስጥተቆራርሶ በተሰጣቸው ክልል ወይም አጥር/ በረት/ውስጥ የራሳቸውና የእኔ የሚሉት የሥልጣን ባለቤትነት ሲኖራቸው፣ ዐማራው ይህ መብትና ሥልጣን የለውም፡በነዚያ ክልሎች የሚኖሩ ነገዶችና ጎሳዎችም እንደዐማራውሁሉ ማሉ መብት የላቸውም፡ የዚህን ተጨበጭዕውነታ ለማወቅና ዐማራውበሁሉም ደረጃ አገር የለሽ መሆኑን በሕገ-መንግሥት የተረጋገጠስለመሆኑ፣ የ9ቱን ክልላዊ መንግሥት ተብየዎች ሕገ-መንግሥት ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚሉ አንድባንድ መመልከቱ ሐቁን እንድንረዳ ያስችለናል።

## 2 የክልል መንግሥታት ሕገ-መንግሥቶች የሥልጣን ባለቤትነት የሰጡት ለማን ነው?

የክልል መንግሥታት፣ በየክልላቸው፣ የሥልጣን ባለቤትነት የማን እንደሆነ መብትና ዕውቅና የሚሰጠው የክልሉ ስም ማጠሪያ ለሆኑት ነገዶች ነው። በዚህም መሠረት በትግራይ ክልል ባለቤቱ ትግራዋይ፣ በኦሮሞ፦ ኦሮሞ፦ በሶማሊ፣ ሶማሌ፣ በቤንሻንጉል-ጉምዝ፣ በርታ፣ ጉሙዝ፣ ሽናሻ ፣ ማኦና ኮሞ፤ በሐረሪ፣ ሐረሪ (አደሬ)፣ በአፋር አፋሮች፣ --ወዘተ ሲሆኑ፣ ከነዚህ በተቃራኒው በዐማራና በጋምቤላ፣ በክልሉ የሚኖሩ ብሔር/ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ናቸውይላል። ለምሳሌ በሐረሪ ክልል ተብየ፣ የኦሮሞና ዐማራ የሕዝብ ቁጥር ከሐረሪዎቹ ከፍተኛ ነው። ይሁንና በሐረሪ ሕገ-መንግሥት ሐረሪውንና ኦሮሞውን ሲያውቅ፣ ዐማራውን ከበር ውጪይጥለዋል። ድሬደዋ ዐማራ፤ ኦሮሞና ሶማሊውየሞገሰ ቁጥር ሲኖራቸው፣ ሕገመንግሥቱ ለኦሮሞና ለሱማሌው እውቅና ሲሰጥ፣ ዐማራውን ከበር ውጪ ይጥለዋል። ቤኒሻንጉል የዐማራውቁጥር ታላቅ ነው። ግን እውቅና የለውም፡ ኦሮሞውስጥምተማሳሳይ ነው። ለዐማራ ክልል ብለው ባጠሩለትም ግዛት ውስጥ፣ ለዐማራው ለሌሎች የሰጡትን ዓይነት የብቻ ባለቤትነት ሲነፍጉት ይታያል።

የፌደራል ሕገ-መንግሥቱ ወደየ ክልሎቹ ሲወርድ፣ እያንዳንዱ ነገድና ጎሣ ዐማራን ተከታትሎ እንዲያጠፋ በዕቅድ የተያዘ በሚሆኑ፣ ዐማራው ከየክልሎቹ የሥልጣንና የመብት ባለቤትነት መብት እንዳይኖረው ተደርጓል። ባለመብቶቹ የየክልሎቹ ስሞች ማጠሪያ እንዲሆን ማለስ የፈቀደላቸው እንዲሆኑ ተደርጓል። በዘጠኙ ክልሎች የሚኖሩና የክልሉ ባለመብትና ባለሥልጣን ያልሆኑ የሌሎች ነገድና ጎሳዎች አባሎች፣ በዚያ ክልል መኖር የሚቻሉት፣ የክልሉ ባለቤት እንዲሆኑ መብትና ሥልጣን የተሰጣቸውነገዶች ሚልካምፈቃድ ብቻ ነው። እነርሱ ካልፈቀዱ ማጤእና ሌላምስምበማስጠት ባሻቸው ጊዜ ሊያባርሯቸው ይችላሉ። የዐማራው ከቤንሻንጉል ጉምዝ፣ ከጅማዞን፣ ከወለጋ፣ ከኢሉባቡር፣ ከሐረርጌ ወዘተ በተከታታይ እንዲባረር የተደረገው፣ የየክልሉን ሕገ-መንግሥት መሠረት በማድረግ ነው። ምክንያቱም በክልሉ ሕገ-መንግሥት ዐማራው የመብትና የሥልጣን ባለመብት አይደለም፡ ዐማራው አገሩን ተቀምቷል። እንደወራሪና ማጤተቆጥሯል። ነፍጠኛ፣ ትምክህተኝ፣ ገዥ መደብና ጨቋኝ ብሔር ተብሎ ተፈርጆ እንዲጠፋ ተፈርዶበታል። ዐማራው በፌደራሉም ሆነ በክልል ሕገ-መንግሥት ተብየዎች አገር አልባ ተደርጓል። እንደማጤ ባይተዋር፣ ሲከፋም እንደ ወራሪና ቅኝ ገዥ ተቆጥሮ በያለበት እየተዋከበና የዘር ማጥፋት ወንጀል እየተፈጸማባት መሆኑን ማጤንና ለዚህ የሚሞጥን ትግል ለማድረግ ምክንያቶች መደርደር አሻሻም፡ «ዉኃን ከጥሩ፣ ነገርን ከሥሩ» እንዲሉ፣ እያንዳንዱ የክልል ሕገመንግሥት ምን እንደሚል አንድባንድእንሚልከት፤

**2.1 የዐማራ ብሐራዊ ክልላዊ ሕገ-መንግሥት፦**

«**የአማራ ብሐራዊ ክልል ሕገ-መንግሥት**» በአዋጅ ቁጥር 2/1988 የተመሠረተውን በ1994 በተሻሻለውና በአቶ ዮሴፍ ረታ ፊርማሕግ ሆነ ውበፀደቀውሕገ-መንግሥት መግቢያ ላይ እንዲህ ይላል።

« እኛ የአማራ ብሐራዊ ክልል ሕዝቦች፦

«**ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየው ጨቋኝ ሥርዓት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችን አፍኖና በተዛባ** ኢኮኖሚና ማህበራዊ ፖሊሲዎች ለድህነትና ለኋላ ቀርነት ዳርጎን መቆየቱ በጠቅላላ እድገታችን ላይ ያደረሰውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለማስወገድ በማሻት፤

«በአብዛኛው የአገራችን ብሔር- ብሔረሰቦች ላይ **ሲፈጸም በቆየው አስከፊ ብሔራዊ ጭቆና ምክንያት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የጉዳቱ ሰላባዎች ሆነን መቆየታችን** በማያዳግም ሁኔታ ማታረም እንዳለበት በማምን፣

«ማለው የአገራችን ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ለዘመናት ባካሄዱት አኩሪ ተጋድሎ የነበረው ኋላቀርነትና አፋኝ ሥርዓት ተገርስሶ አገራችን ኢትዮጵያ የግለሰቦችና የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ጨምሮ የሁሉም ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሙሉ የተከበሩባትና በአጠቃላይ የሕግ የበላይነት የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መሆኗ የጋራ ዕድገታችን መፍጠን ያለውን ጠቀሜታ በማገንዘብ፤

«እኛ በአማራ ብሄራዊ ክልል የምንገኝ ህዝቦች ለተፋጠነ ኢኮኖሚያዊ እድገት፣ ለዘላቂ ሰላምና ለዳበረ ዲሞክራሲ የምንበቃው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት መሠረት ያደረገ ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘበና የብሔራዊ ክልሉ ህዝቦች የተከበሩልንን ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ባልተሸራረፈ ሁኔታ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችለን የራሳችን ሕገ-መንግሥት ሲኖረን እንደሆነ አጥብቀን በማመን፣ --ወዘተ»

እነዚህን እንደ ወሣኝ ዓላማዎችና እንደ መነሻ ሀሳብ ይዞ፣ በምዕራፍ ሁለት፣ **በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ «የአማራ ክልል ሕዝቦች የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ የበላይ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው**« ይላል።

ይህ አንቀጽ በቁጥሩም ሆነ በታሪኩ ከፍተኛ ለሆነው ዐማራ ለኦሮሞው የሰጠውን ዓይነት በክልሉ የሥልጣን የበላይነት እንዲኖረው አይፈቅድም። የሚፈቅደው፣ ለክልሉ ሕዝቦች ነው። ሕዝብ ሲልም በመጀመሪያ በአዕምሮአችን የሚደቀነው፤ ዐማራው በራሱ በወያኔው ሕገ-መንግሥት ዕውቅና ለተሰጠው የብሔር ወይም የብሔረሰብ የዕድገት ደረጃ ያልደረሰ፣ በዝቅተኛ የማኅበረሰብ የዕድገት ደረጃ የሚገኝ ነው የሚለው ትርጉም ነው። ሌሎቹን አብዛኛዎቹን ክልሎች ብሔር/ ብሔረሰብ ሲል፣ ዐማራውን ሕዝብ በማለት ያሳንሰዋል። በሁለተኛ ደረጃ፣ የዐማራው ክልል በኢትዮጵያ የሚገኙ የማናቸውም ነገዶች በሥራ፣ በንግድ፣ በእርሻ ወዘተ የፈለጉትን ሞያ ጠውእንዲይዙ፣ ዐማራውን እንዲያፈናቅሉ ለማምቻቸት፣ ሕዝቦች የሚለውን ቃል ማጠቀም ዐማራውን የማጥፊያ ዘዴ እንዲሆን የተዘየደ ዘዴ እንደሆነ ያስገነዝባል። በሌላ በኩል ኢትዮጵያ አንድ ዜጋ እንዳልመሠረተች ሁሉ፣ ሕዝቦች በማለት የማላያያ መንገድ እንዳዘጋጀ ሁሉ፣ በዐማራው ክልል ተብየው ያሉትንም ነገዶች ከዐማራው ለማጠነል ሕዝቦች ብሏቸዋል። በዚህ የማጠል ሥልቱም፤ አገውን፣ ከጎጃም ዐማራ፣ ቅማንትን ከጎንደር ዐማራ፣ የከምሲ ኦሮሞዎችን ከወሎ ዐማራና ከአፋር ሕዝብ በማጠል የዐማራው ጠላቶች ሆነው እንዲቆሙ እያደረገ ነው።

ከላይ በሕገ-መንግሥቱ መግቢያ የተጠቀሱት ሐረጎችና ቃሎች ማለትም «**ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየ ጨቋኝ ሥርዓት፣ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችን አፍኖ፣ በተዛባ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ፖሊሲዎች ለድህነትና ኋላቀርነት ዳርጎን፤ በአብዛኛው የአገራችን ብሔር ብሔረሰቦች ላይ ሲፈጸም የቆየው አስከፊ ብሔራዊ ጭቆና፣ ---ብሔር ብሔረሰቦች ለዘመናት ባካሄዱት አኩሪ ተጋድሎ፣ የነበረውን ኋላቀርና አፋኝ ሥርዓት ተገርሥሦ---የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ ማንጠል ያለው መብት ያላዳች ቅድመ ሁኔታ የተጠበቀ ሆኖ፣ የተከበሩልንን ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች ባልተሸራረፈ ሁኔታ በሥራ ላይ ለማዋል --**» የሚሉት የሁሉም ሕገ መንግሥቶች ዋና እና መሠረታዊ ጉዳዮች ሆነው ተጠቅሰዋል። እነዚህ ሁሉ የውግዘት ሀረጎች በቀጥታ የሚማለከቱት ዐማራውን ነው። የዐማራ ክልል ተብሎ በስሙ ለተሰየመው ክልልም፤ የሥልጣን ባለቤቱ ዐማራው አይሁን እንጂ፣ የሁሉም ሕገ-መንግሥቶች መሠረት የሆኑት ሀሳቦች የዚህ ክልል ሕግ ገዥ ሀሳቦች ሆነው ተገልጸዋል። ይህ ምን ማለት እንደሆነ ለጠየቀ ሰው፣ መልሱ አጭርና ግልጽ ነው። ዐማራው ራሱን በራሱ እንዲያጠፋ፣ በራሱ ላይ ዘመቻ እንዲከፍት ወዶ የተቀበለው ሕገ-መንግሥቱ እንደሆነ ሚረጋገጨነው። ለዚህም ነው በትግሬ-ወያኔ አገዛዝ፣ በክልሉ አውራ ጎዳናዎች በተሠሩ ቅስቶች፣ ፋሲል ግንብ ሳይቀር፣ «ዐማራው ትምክህተኛ ነው! ትምክህተኝነትን አጥብቀን እንዋጋለን! ዐማራው ጨቋኝ ብሔር ነው! ጨቋኝ እና ጠባብ ብሔርተኝነትን እንዋጋለን!» የሚሉ ሚክሮች ተወጥረው ተሰቅለው፣ ዐማራውራሱን በራሱ ሲያዋርድ፣ ለተገዥነትና ለጥፋት ኅሊናውን እንዲያዘጋጅ የሥነ ልቦና ጦርነት ተከፍቶበት የነበረውና ያለው። በዚም የተነሳ፣ ዐማራው የራሱ የሆነ ክልልም ሆነ አገር እንዳይኖረው ተደርጓል። ይህ ሕዝብ እየተፈጸመበት ያለውን ግፍና ጥቃት የቱን ያህል የሠፋና የከፋ እንደሆነ ለማየት በራሱ ክልል የተሰየመውን አካባቢ እና የነዋሪዎቹን ማንነት ከራሳቸው ከወያኔዎች ጥናት ተነስተን እንመልከት።

እንደ አገሪቱ ማዕከላዊ ስታትስቲክ ማሥሪያ ቤት የ2007 እኤአ መረጃ መሠረት፣ የክልሉ የቆዳ ሥፋት **154,708.96** ስኩዌር ኪሎ ሜትር ወይም **59,733.46** ስኩዌር ማይል ነው፡፡ የክልሉ ሕዝብ ብዛት **17,221,976** ነው፡፡ በአንድ ስኩዌር ኪሎሜትር ውስጥ የሚኖረው የሰዎች ብዛት **108.2** ነው፡፡ ከጠቅላላው የክልሉ ነዋሪ ውስጥ **8,641,580** ወንዶች ሲሆኑ፣ **8,580,396** ሴቶች ናቸው፡፡ ከዚህ ውስጥ በከተሞች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት **2,112,595** ወይም ከጠቅላላ ሕዝቡ **12.27** በመቶ ሲሆን፣ ቀሪው ማለትም **15,109,381ዱ(87.73%)** የገጠር ነዋሪ ነው፡፡ በክልሉ ውስጥ በከተማም በገጠር ምያለው የቤተሰብ ወይምጢስ ብዛት**3,983,786** ነው፡፡ ይህም በአማካኝ ባንድ ቤተሰብ ውስጥ 4.3 ሰዎች አሉ ማለት ነው፡፡

እንደ ማዕከላላዊ ስታትስቲክ የ2004 መረጃ መሠረት፣ በዐማራ ክልል ከሚኖረው የገጠር ነዋሪ ሕዝብ የንፁሕ ውኃ ተጠቃሚው ቁጥር ከመቶ **19.89** ብቻ ነው፡፡ 80.11 የሚሆነው የንፁሕ ውኃ ተጠቃሚ አይደለም፡፡ በከተማ የሚኖረው**91.8** የሚሆነው የንፁሕ ውኃ ተጠቃሚ እንደሆነ መረጃው ያሳያል።

በሌላ በኩል እንደ ማሥሪያ ቤቱ የ2005 እኤአ መረጃ መሠረት፣ ከጠቅላላው የዐማራ ክልል ነዋሪ ሕዝብ ውስጥ ከመቶ **17.5** የሚሆነው ከድህነት ወለል በታች በሆነ አስከፊ የድህነት ኑሮ የሚኖር ነው፡፡ ማንበብና መጻፍ ይችላል የተባለው ከሕዝቡ **54%** በመቶ ወንዶች፣ **25.1** ሴቶች መሆናቸውን መረጃው ይጠቁማል። በሕፃናት ጤንነት ረገድ ከ1000 (ከሺ) 94 የሚሆኑት እንደተወለዱ ይሞታሉ። ይህም ከአጠቃልይ የአገሪቱ በሺ 77 ከሆነው ጋር ሲነፃጸር፣ የዐማራው የሕፃናት ሞት፣ በሺ **14** እንደሚበልጥ ያሳይል።

ቢያንስ በክልሉ የባለቤትነት መብት የተነፈገውእና መብትና ሥልጣኑ ለክልሉ ሕዝቦች ነው የተባለትን ኢ-ፍትሐዊነት ብቻ ሳይሆን፣ ዐማራውን ነጥሎ ለማጥፋት የተጠሚደ ወጥመድ መሆኑን ለማሳየት በክልሉ የሚኖሩትን ነገዶችና ጎሳዎች ብዛት ማየቱ ለተነሳንበት ማንደርደሪያ ሀሳብ ዋና ቋጠሮ እንደሚሆን ለማሳየት ይረድል።

**በዐማራ ክልላዊ መንግሥት የሚኖሩ ነገዶች ሥብጥርና ብዛት ማሳያ ሠንጠረዥ(1)፤**

| ተራ ቁጥር | ነገዶች | ዘመን እኤአ 1994 | ዘመን እኤአ 2007 |
|---|---|---|---|
| 1 | ዐማራ | 91.2% | 91.47% |
| 2 | አገው | 2.7% | 3.46% |
| 3 | ኦሮሞ | 3% | 2.62% |
| 4 | አጋዊ/ቅማንት | 1% | 1.39% |
| 5 | አርጎባ | === | 0.41% |

ከሁለቱም ዘመኖች የሕዝብ ብዛት ስንማለከት ዐማራው በሕዝብ ብዛቱ ከፍተኛ ብቻ ሳይሆን፣ የክልሉ ባለቤትነቱ የርሱ መሆኑን ያሳያል። በየትኛውም መመዘኛ ቢለካ የሥልጣን ባለቤቱ ዐማራው ለመሆኑ አንዳች ጥርጥር የለም፡፡ ሆኖም፣ ዐማራው ለማጥፋት በሚፈለጉና፣ የዐማራው ክልል ባለቤት የሌለው፣ ሁሉም ያሻውን እንዲያደርግ የተፈረደበት በመሆኑ፣ በሕገ-መንግሥቱ የባለቤትነት ሥልጣን እንዳይኖረው ተደርጓል። በራሱ ልጆችም እንዳይመራ ሆኗል። ገዥዎቹ ትግሬዎቹ፣ ኤርትራውያኑ፣ ኦሮሞዎቹ፣ ሲዳማዎቹ ወዘተ ሆነዋል። እናም ዐማራው አገር አልባ ነው፡፡ የዐማራው መሠረታዊ ጥያቄም ጎልውናውን የማስከበርና የተነጠቀውን የአባቶቹን አገር የማስማለስ ጥያቄ ነው፡፡

## 2.2. የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት :-

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፤የካቲት 9/90 የፀደቀውንና ሲሠራበት የቆየውን ሕገ-መንግሥት ሚያዝያ---ቀን/1994 በተሻሻለውና በአቶ እስማኤል ዓሊሲሮ ፊርማ ሕግ ሆነው በፀደቀው ሕገ-መንግሥት መግቢያ ላይ እንዲህ ይላል።

«እኛ የአፋር ሕዝብ **ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየውአፋኝ ስርዓት** ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችን ታፍነው በተዛቡ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች ለድህነትና ኋላ ቀርነት አጋልጦን መቆየቱ በአጠቃላይ ዕድገታችን ያደረሰውአሉታዊ ለማስወገድ በሚለግ፤

«ማለውየአገራችን ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባካሄዱት አኩሪ ተጋድሎአድኃሪውንና አፋኙ ሥርዓት በሚያስተማምን ሁኔታ ተደምስሶ ኢትዮጵያ አገራችን የግለሰብ መብቶችና የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል የተከበሩባት አጠቃላይ የሕግ የበላይነት የነገሠበት ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መሆንዋ የጋራ ዕድገትን ለማፋጠንና አንድ የጋራ ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰብ ማፃጽ ያለውን ጠቀሜታ በማገንዘብ፤

«የአፋር ሕዝብ ያለፉት **የኢትዮጵያ ጨቋኝ ሥርዓቶችን ለማደምሰስ** ወደር የሌለው ማስዋዕትነት ከከፈለበት ምክንያቶች አንዱና ዋናውሁሉም ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸውየተከበሩ፣ ሕዝቦች በሕገ-መንግሥቱና በሱ ብቻ የምትመራ ዲሞክራሲያዊት ሀገር እንድትሆን፣በማለት በአብዛኛው የሀገራችን ብሄር ብሄረሰቦች ሕዝቦች ላይ ይፈጸም በነበረው አንገፍጋፊ ጭቆና ተጎጂ ሆነን መቆየታችን በሚያዳግምሁኔታ ማታረምእንዳለበት በማምን፣ ---ወዘተ»

እነዚህን እንደ ወሣኝ ዓላማዎች እና እንደ መሻ ሀሳብ ይዞ፣ በምዕራፍ ሁለት የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ **8 ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ «የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት የበላይነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአፋር ሕዝብ የብሔራዊ ክልሉ መንግሥት የበላይ ሥልጣን ባለቤት ነው።» ይላል።**

እነዚህ ከዚህ በላይ የሰፈሩት መሠረታዊ ሀሳቦች በዐሚራም ሆነ በሌሎች ክልላዊ መንግሥታት ሕገ-መንግሥት ተብየ የሰፈሩ ናቸው። ዋና ትኩረታቸውም ዐሚራውነ ጥሎ ማምታ ነው። እየተደረገ ያለውም ይኸውነው። ልዩነት ያለው፣ የአፋር ክልል ግዛት ባለመብቱና የሥልጣን ባለቤቱ የአፋር ነገድ ነው። በክልሉ የሚኖሩ ሌሎች ነገዶች የባለቤትነትም ሆነ የሥልጣን ይገባናል መብት ፈጽሞ የሌላቸውሚሆኑ ነው። ክልሉ የራሱ ባለቤት አለው። የአፋር ነገድ!

እንደ አገሪቱ ማዕከላዊ ስታተስቲክ ማሥሪያ ቤት እኤአ የ2007 ሚረጃ መሠረት፣ የክልሉ የቆዳ ሥፋት በግምት **96,707** ስኩዌር ኪሎ ሜትር ነው።የክልሉ ሕዝብ ብዛት እኤአ 2007 ሚረጃ መሠረት **1,390,273** ነው። በአንድ ስኩዌር ኪሎሜትር ውስጥየሚኖረውየ ሰዎች ብዛት **14.38** ነው። ከጠቅላላውየክልሉ ነዋሪ ውስጥ **775,117** ወንዶች ሲሆኑ፣ **615,156** ሴቶች ናቸው።ከዚህ ውስጥ በከተሞች የሚኖረውሕዝብ ብዛት **185,135** ወይምከጠቅላላ ሕዝቡ **13.32** በመቶ ሲሆን፣ ቀሪውማለትም **409,123**ቱ (**29.43**%) የገጠር ነዋሪ ወይምዘላን ነው። በክልሉ ውስጥበከተማምበገጠርምያለውየ ቤተሰብ ወይምጢስ ብዛት **247,255** ነው። ይህምበአማካኝ ባንድ ቤተሰብ ውስጥበከተሞች **5.6** ሰዎች ሲኖሩ፣ በገጠር **6** ሰዎች ባንድ ቤተሰብ ውስጥ ይገኛል።

እንደ ማዕከላላዊ ስታተስቲክ የ2004 እኤአ ሚረጃ መሠረት፣ በአፋር ክልል ከሚኖረውየገጠር ነዋሪ ሕዝብ የንፁሕ ውኃ ተጠቃሚውቁጥር ከመቶ **48.57** ብቻ ነው። ከዚህ ውስጥ **26.89** በመቶውከተሜ ሲሆን፣ የቀረው **78.11** ከመቶው የገጠር ነዋሪ ነው። ከጠቅላላ ነዋሪው **54.43** ከመቶውየንፁሕ ውኃ ተጠቃሚ እንዳልሆነ ሚረጃዎች ያሳያሉ።

በሌላ በኩል እንደ ማሥሪያ ቤቱ የ2005 እኤአ ሚረጃ መሠረት፣ ከጠቅላላውየአፋር ክልል ነዋሪ ሕዝብ ውስጥ ከመቶ **67.3** ከመቶ የሚሆነ ውከድህነት ወለል በታች በሆነ አስከፊ የድህነት ኑሮ የሚኖር ነው። መጻፍና ማንበብ ይችላል የተባለው ከሕዝቡ **27%** በመቶ ወንዶች፣ **15.6** ሴቶች መሆናቸውን ሚረጃው ይጠቁማል። በሕፃናት ጤንነት ረገድ ከ1000 (ከሺ) **61** የሚሆኑት እንደተወለዱ ይሞታሉ። ይህም ከአጠቃልይ የአገሪቱ በሺ 77 ከሆነ ውጋር ሲነፃጸር፣ የአፋር የሕፃናት ሞት፣ በሺ 16 እንደሚያንስ ያሳይል።

**የአፋር ክልላዊ መንግሥት የሚኖሩ ነገዶች ሥብጥርና ብዘት ማሳያ ሠንጠረዥ(2)፤**

| ተራ ቁጥር | ነገዶች | ዘመን 1994 እኤአ | ዘመን 2007 እኤአ |
|---|---|---|---|
| 1 | አፋር | 91.8% | 90.3% |
| 2 | ዐማራ | 4.5% | 5.22% |
| 3 | አርጎባ | 0.9% | 1.55% |
| 4 | ትግሬ | 0.8% | 1.15% |
| 5 | ኦሮሞ | 0.8% | 0.61% |
| 6 | ወላይታ | 0.5% | 0.59% |
| 7 | ሐዲያ | 0.2% | 0.18% |

እኤአ በ1994 በተደረገው ቆጠራ የአፋር ክልል ሕዝብ ቁጥር **1,106,383** እንደሆነ ተዘግቧል። ከዚህ ውስጥ **626,839** ወንዶች፣ **479,544** ሴቶች ናቸው። ከጠቅላላው ሕዝብ **85,879** ወይም **7.76**ቱ የከተማ ነዋሪዎች ሲሆኑ የቀረው ዘላን ነው። በክልሉ ከሚኖሩት ዋና ዋና ነገዶች ውስጥ ከላይ በሠንጠረዡ ተጠቅሰዋል። በከተሞች ከሚኖረው ሕዝብ ዐማራ በቁጥሩ ከፍተኛ ነው። ከከተሞች ሕዝብ **42.5** ከመቶው ዐማራ ነው። አፋር ከመቶ **32.6** ከመቶ በማያዝ በሁለተኛ ደረጃ ይሚራል። ትግሬ **7.8**% ፣ ኦሮሞ **6.7%፣** አርጎባ **2.6%፣** ወላይታ **2.2** % በማያዝ በአራተኛ፣ በአምስተኛ እና በስድስተኛ ደረጃ ይገኛሉ።

ከሠንጠረዡ ለሚረዳት እንደሚቻለው፣ በአፋር ክልል 7 ነገዶች ይገኛሉ። በሕገ መንግሥቱ ግን የክልሉ ባለቤት የአፋር ነገድ ነው። ከሁሉምበላይ በክልሉ ከሚገኙት ከተሞች ዐማራውከፍተኛ ቁጥር እያለው፣ ተወካዮችን የማሚረጥም ሆነ የመሚረጥ መብት የለውም። በክልሉ የሚገኙ፣ ኢትዮጵያ አገራችን ናት ብለውለዘመናት በትናንቱ ወሎ ክፍለሀገር፣ በዛሬውየአፋር ክልል የኖሩ ነገዶች፣ የትግሬ-ወያኔ ውሚ ማለስ ዜናዊ ባዘጋጀውሕገ-መንግሥት መሠረት፣ በክልሉ መኖር የሚችሉት በአፋር ሕዝብ ሜልካም ፈቃድ ብቻ ነው። በዚህምየተነሳ ነው፣ የዐማራውን ነገድ ተወላጆች በክልሉ ተደጋጋሚሚዜናቀልና የዘር ጥቃት ሰላባዎች የሆኑት።

**2.3 የሶማሊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት፡-**

የሶማሊ ክልላዊ መንግሥት ሚያዝያ ወር 1994 ዓምበፀደቀውሕገ-መንግሥት እንዲህ ይላል፤

«እኛ የሶማሊ ሕዝብ በእኛና በሌሎች የአገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ላይ ተንሰራፍቶ የነበረውየጭቆና ሥርዓት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችን አፍኖ፣ በተዛባ ፖለቲካ ፣ ኢኮኖሚ ማኅበራዊ ፖሊሲዎች በሙተብተብ ለድህነትና ለኋላቀርነት ዳርጎን በገዛ ሀገራችን እንደሁለተኛ ዜጋ በመቆጠር የስቆቃ ኑሮ እንድናሳልፍ ሚድረጉን በሚቃወምና በሚያዳግም ሁኔታ ሚታረም እንዳለብት በማምን፤

«ማለው የአገራችን ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ለዘመናት ባካሄዱት አኩሪ ተጋድሎ የነበረው ኋላቀርነትና አፋኝ ሥርዓት ተገርስሶ አገራችን ኢትዮጵያ የግለሰቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ ማንጠል ጨምሮ የሁሉምብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሙሉ የተከበሩባትና በአጠቃላይ የሕግ የበላይነት የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሚሆኗ የጋራ ዕድገታችን ሜፋጠን ያለውን ጠቀሜታ በማንዘብ፤ ወዘተ»

እነዚህን ዓላማዎች እና ሜዳረሻ ሀሳቦች በማያዝ፣ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) ላይ« **የሶማሌ ህዝብ የክልሉ የበላይ የሥልጣን ባለቤት ነው።** » ይላል። ይህም ማለት የክልሉ ባለቤትና ባለሥልጣን የአፋር ነገድ ብቻነው። ሌሎቹ እንደ ኢትዮጵያዊ ዜጋ አይቆጠሩም። ምንምዓይነት መብትና ጥቅምየላቸውም።

እንደ አገሪቱ ማዕከላዊ ስታተስቲክ ማሥሪያ ቤት እኤአ የ2007 ሚረጃ ማሠረት፣ የክልሉ የቆዳ ሥፋት በግምት **279,252** ስኩዌር ኪሎ ሜትር ነው፡ የክልሉ ሕዝብ ብዛት እኤአ 2007 ሚረጃ ማሠረት **4,445,219** ነው፡ በአንድ ስኩዌር ኪሎ ሜትር ውስጥ የሚኖረው የሰዎች ብዛት **15.9** ነው፡ ከጠቅላላው የክልሉ ነዋሪ ውስጥ **2,472,490** ወንዶች ሲሆኑ፣ **1,972,729** ሴቶች ናቸው፡ ከዚህ ውስጥ በከተሞች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት **623,004** ወይም ከጠቅላላ ሕዝቡ **14.02** በመቶ ሲሆን፣ ቀሪው ማለትም **1,687,858**ቱ **(37.9%)** የገጠር ነዋሪ ወይም ዘላን ነው፡ በክልሉ ውስጥ በከተማም በገጠርም ያለው የቤተሰብ ወይም ጢስ ብዛት **687,986** ነው፡ ይህም በአማካኝ ባንድ ቤተሰብ ውስጥ **6.8** ሰዎች ይገኖራሉ።

**የሶማሊ ክልላዊ መንግሥት የሚኖሩ ነገዶች ሥብጥርና ብዛት ማሳያ ሠንጠረዥ(3) ፤**

| **ተራ ቁጥር** | **ነገዶች** | **ዘመን 1994 እኤአ** | **ዘመን 2007 እኤአ** |
|---|---|---|---|
| 1 | ሶማሊ | 96.23% | 97.2% |
| 2 | ዐማራ | 0.69% | 0.66% |
| 3 | ኦሮሞ | 2.25% | 0.46% |
| 4 | ከውጭ የተወለዱ ሶማሊዎች | ==== | 0.20% |
| 5 | ጉራጌ | 0.14% | 0.12% |

እኤአ በ1994 በተደረገው ቆጠራ የሶማሊር ክልል ሕዝብ ቁጥር 3,439,860 እንደሆነ ተዘግቧል። ከዚህ ውስጥ **1,875,996** ወንዶች፣ **1,563,864** ሴቶች ናቸው፡ ከጠቅላላው ሕዝብ **492,710** ወይም **13.94**% የከተማ ነዋሪዎች ሲሆኑ የቀረው ማለትም **86.06**% ዘላን ነው፡ ባንድ ቤተሰብ ውስጥ ያለው የሰው ብዛት **6.6** ነው፡ እንደ 2004 እኤአ ሚረጃ ማሠረት፣ ከሶማሊ ክልል ሕዝብ የንፁሕ ውኃ አገልግሎት ተጠቃሚው ከሕዝቡ **38.98** ቱ ብቻ ነው፡ ከዚህ ውስጥ **21.32** ከገጠር ነዋሪዎች ሲሆኑ፣ **77.21**ዱ ከተሜዎች ናቸው፡ እንደ ማዕከላዊ ስታተስቲክስ የ2005 እኤአ ሚረጃ ማሠረት፣ ከነዋሪው **71.8** በመቶው ከድህነት ወለል በታች ባለ የድህነት አረንቋ ውስጥ የሚኖር ነው፡ ከሕዝቡ ወንዶች **22** በመቶ፣ ሴቶች **9.8** በመቶ ማንበብና መጻፍ ይችላሉ። የሕፃናት ሞት በሺ 57 ነው፡ ይህም ከአገር አቀፉ በ**20** ያነሰ ነው፡

ከሠንጠረዡ ለሚረዳት እንደሚቻለው፣ በሶማሊ ክልል 5 ነገዶች ይገኛሉ። በሕገ መንግሥቱ ግን የክልሉ ባለቤት የሶማሊ ነገድ ነው፡

**የሶማሊ ሕዝብ ዕድገት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዕድገት አንፃር፣ (ሠንጠረዥ4)**

| ዓመት ምህረት እኤአ | የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት | የሶማሊ ሕዝብ ብዛት | ከኢትዮጵያ ሕዝብ አንፃ በመቶኛ | |
|---|---|---|---|---|
| 2007 | 73,439,147 | 4,439,147 | 6.1% | |
| 2017 | 84,320,987 | 5,148,989 | 6.11% | |
| 2013 | 86,613,986 | 5,318,00 | 6.14% | |
| | | | | |

**2.4 የጋምቤላ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት፡-**

የጋምቤላ ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ታህሳስ 9ቀን 1995 ዓም በጸደቀው ሕገ መንግሥት እንዲህ ይላል።

«እኛ የጋምቤላ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሀገራችንና በክልላችን ተንሰራፍቶ የቆየውን የጭቆና ስርዓት ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻችን አፍኖ በተዘቡ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፖሊሲዎች በማከተል ለድህነትና ለኋላቀርነት ዳርጎን መቆየቱ በሚያዳግም ሁኔታ ማታረም ያለበት መሆኑን በማመን የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን በነፃ

ፍላጎታችን በክልላችን የሕግ የበላይነት ለማክበርና ለማስከበር ባለን ጽኑ እምነታችን ላይ በመመርኮዝ ክልላችን በጋራ ለማንባት የግለሰብን የብሔረሰቦችን ሃይማኖት ጠቃሚባህሎና ልምዶች ምንምልዩነት ሳይደረግባቸውእንዲራመዱ ዓላማችን በመሆኑ፤

«እኛ የአኙዋክ፣ የኑዌር፣ የመዠንገር፣ የኦፖና ኮሞ ብሔረሰቦች ለተፋጠን ኢኮኖሚዕድገት ለዘላቂ ሰላምና ዲሞክራሲ የምንበቃውየኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን ሕገ መንግሥት መሠረት ያደረገና የክልላችን ተጨበጭሁኔታ ያገናዘበ የክልላችን ሕገ-መንግሥት ሲኖረን መሆኑን በውል በሚዳት፣ » ይልና፤

እነዚህን ዓላማዎች መሻ በማድረግ፣ በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 9(1) **ላይ «የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል ሕዝብየክልሉ ብሔራዊ መንግሥት የበላይ የሥልጣን ባለቤት ነው፡፡»** ይላል፡፡

በዚህ ክልል፣ ከላይ በተገለጸውአንቀጽ እንደሚያስረዳው፣ ክልሉን በብዙ ሕዝቦች ጠርቶ፣ መብቱን ለአንድ ሕዝብ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ የክልሉ ነዋሪም እንደ ዐማራው ክልል ሁሉ ፣ በዕድገት ደረጃውብሔር/ብሔረሰብ ያልደረሰ ዝቅተኛ ማኅበረሰብ ደረጃ እንዳለ፣ አንድነገድ አድርጎ ይቆጥረዋል፡፡ ከመግቢያውላይ እኛ የአኙዋክ፣ የኑዌር፣ የመዠንገር፣ የኦፖ እና ኮሞ ብሔረሰቦች ብሎ የጠራውን ከታች ሕዝቦች በማለት ያሰንሳቸዋል፡፡ ይህምሆን ተብሎ ለትርጉም አሻሚ በማድረግ፣ ሜሬቱን ለትግሬ ጀኔራሎች ለማቀራመት እንዲመች ተደርጎ የተዘጋጀ እንደሆን ማናዘብ ይቻላል፡፡ ይህምበሚሆኑ ነውበአኙዋክ ነገድ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲፈጸም የተደረገው፡፡ ከመዠንገር፣ ከኦፖና ከኮሞ ነገዶች በቁጥሩ ልቆ ለማ ኘው ዐማራ የባለቤትነት መብት አልሰጠውም፡፡ ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድርም ዕውቅና ነፍጎታል፡፡ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ልብ ያለውልብ ይለዋል፡፡

እንደ አገሪቱ ማዕከላዊ ስታተስቲክ ማሥሪያ ቤት እኤአ የ2007 ሚጃ መሠረት፣ የጋምቤላ ብሔራዊ ክልል የቆዳ ሥፋት **29,788.22** ስኩዬር ኪሎ ሜትር ነው፡፡ የክልሉ ሕዝብ ብዛት **307,096** ነው፡፡ በአንድ ስኩዬር ኪሎ ሜትር ውስጥ የሚኖረውየሰዎች ብዛት **10** ነው፡፡ ከጠቅላላውየክልሉ ነዋሪ ውስጥ **159,787** ወንዶች ሲሆኑ፣ **147,309** ሴቶች ናቸው፡፡ ከዚህ ውስጥ በከተሞች የሚኖረውሕዝብ ብዛት **77,925** ወይም ከጠቅላላ ሕዝቡ **25.37** በመቶ ሲሆን፣ ቀሪው ማለትም **229,171** ወይም **74.62%** የገጠር ነዋሪ ነው፡፡ በክልሉ ውስጥ በከተማም በገጠርም ያለውየቤተሰብ ወይም ጢስ ብዛት **66,467** ነው፡፡ ይህም በአማካኝ ባንድ ቤተሰብ ውስጥ **4.6** ሰዎች ይገኖራሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ በከተማ**3.8፣** በገጠር ደግሞ**4.9** ሰዎች በቤተሰብ ውስጥ ይኖራሉ፤

**የጋምቤላ ክልላዊ መንግሥት የሚኖሩ ነገዶች ሥብጥርና ብዛት ማሳያ ሠንጠረዥ(3)፤**

| **ተራ ቁጥር** | **ነገዶች** | **ዘመን 1994 እኤአ** | **ዘመን 2007 እኤአ** |
|---|---|---|---|
| 1 | ኑኤር | 39.7% | 46.66 |
| 2 | አኙዋክ | 27.45% | 21.16% |
| 3 | መዠንገር | 5.76% | 4% |
| 4 | ካፍቾ | 4.18% | 5.04% |
| 5 | ሻክቾ | 0.14% | 2.27% |
| 6 | ዐማራ | 7.74% | 8.42% |
| 7 | ኦሮሞ | 6.49% | 4.83% |
| 8 | ከምባታ | == | 1.44% |
| 9 | ትግሬ | = | 1.32% |
| 10 | ሌሎች | 8.68% | 4.86% |

እኤአ በ1994 በተደረገው ቆጠራ የጋምቤላ ክልል ሕዝብ ቁጥር **181,862** እንደሆነ ተዘግቧል። ከዚህ ውስጥ **92,902** ወንዶች፣ **88,960** ሴቶች ናቸው። ከጠቅላላው ሕዝብ **27,424** ወይም **15.08**% የከተማነ ዋሪዎች ሲሆኑ የቀረው ማለትም **154,138** ወይም **84.89**% ገጠሬ ነው። የክልሉ ቤተሰብ ወይም ጢስ ብዛት **35,940** ነው። ባንድ ቤተሰብ ውስጥ ያለው የሰው ብዛት **5.06** ነው። እንደ ማዕከላዊ ስታተስቲክስ የ2005 እኤአ ሚ ጃ መሠረት፣ ከነዋሪው **44%** በመቶው ከድህነት ወለል በታች ባለ የድህነት አረንቋ ውስጥ የሚኖር ነው። ማንበብና መጻፍ የሚችለው ከሕዝቡ ወንዶች **57.5%**፣ ሴቶች **22.8%** ናቸው። የሕፃናት ሞት በሺ **92** ነው። ይህም ከአገር አቀፉ በ**15** የሚበልጥ ነው።

ከሠንጠረዡ ሚረዳት እንደሚቻለው በጋምቤል ክልል ከአሥር በላይ ነገዶች ይኖራሉ። በሕዝብ ቁጥር አንፃራዊ የበላይ ነት ያለው የኑኤር ነገድ ሆኖ፣ ተከዩ የአኙዋክ ነገድ ነው፡ዐሜራ በብዛት በሦስተኛነ ት ደረጃ ይገኛል።

## 2.5 የቤንሻንጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት:-

ኅዳርወር 1995 ዓም ተሻሽሎ እና ገዥ ሕግ ሆኖ በአቶ ያረጋል አይሸሽም ተፈርሞ ሥራ ላይ የዋለው ሕገ -መንግሥት መግቢያ እንዲህ ይላል፤

«እኛ የቤኒሻጉል-ጉሙዝ ክልል ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በጋራ በሚቃቀድና በእኩልነት ላይ ተማሥርተን በአቋቋምነው ክላልችን የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን፣ ኢኮኖሚያዊና ማነበራዊ ዕድገታችን እንዲፋጠን የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን ቋንቋችንን ባህላችንና እድገታችን ይበልጥ ለማጠናከር ማንነታችን ተከብሮ በትግላችንና በከፈልነው ማስዋዕትነት የተገኘውን ዲሞክራሲና ሰላምበዘላቂነት ለሚጋገጥ፤

«እኛ የበርታ፣ የጉሙዝ፣ የሽናሻ፣ የማኦ እና የኮሞ ብሔረሰቦች እና ሌሎች በክልሉ የሚኖሩ ሕዝቦች ለተፋጠነ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ለዘላቂ ሰላምና ዲሞክራሲ የምንበቃው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መሠረት ያደረገና የክልላችንን ተጨባጭ ሁኔታዎች ያገናዘበ ሕገ መንግሥት ሲኖረን ሚሆኑን በውል በሚረዳት፣ » ወዘተ

እነዚህን ዓላማዎች ማሳ በሚድረግ፣ በክልሉ ሕገመንግሥት አንቀጽ 9(1) «**የቤኒሻንጉል-ጉሙዝ ክልል ሕዝብ የክልሉ መንግሥት የበላይ የሥልጣን ባለቤት ነው።**» **ይላል።**

በዚህ አንቀጽ፣ ከጋምቤላ ጋር ሲነፃፀር፣ «የጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል ሕዝብ የክልሉ ብሔራዊ መንግሥት የበላይ የሥልጣን ባለቤት ነው» በሚለው ምትክ፣ የቤንሻጉል ጉሙዝ «--ክልል ሕዝብ የክልሉ የመንግሥት የበላይ የሥልጣን ባለቤት ነው» ይላል። ይህም ማለት ጋምቤላን «ሕዝቦች» ሲል፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝን «ሕዝብ» በማለት አንድ ነገድ እንደሆነ እና የዕድገት ደረጃውም ከብሔረሰብ በታች የሆነ ማነበረሰብ እንደሆነ ይገልፀዋል። ከብዙ ነገዶች ወደ አንድ ነገድ ባለቤትነት ማውረዱን ያሳያል። ይህም ለሕግ ትርጓሜአሻሚከሚሆን አልፎ ተፃራሪ ነው። የክልሉ የሥልጣን ባለቤት ማን ወይም እነማን እንደሆኑ ባለመግለጽ የትግሬ-ወያኔ የፈለገውን እንዲያደርግ ሠፊ ዕድል የሚሰጥ ነው።

እንደ አገሪቱ ማዕከላዊ ስታተስቲክ ማሥሪያ ቤት እኤአ የ2007 ሚጃ መሠረት፣ የክልሉ የቆዳ ሥፋት በግምት **49,289.46** ስኩዬር ኪሎ ሜትር ነው። የክልሉ ሕዝብ ብዛት እኤአ 2007 ሚጃ መሠረት **784,345** ነው። በአንድ ስኩዬር ኪሎሜትር ውስጥ የሚኖረው የሰዎች ብዛት **15.91** ነው። ከጠቅላላው የክልሉ ነዋሪ ውስጥ **398,655** ወንዶች ሲሆኑ፣ **385,690** ሴቶች ናቸው። ከዚህ ውስጥ በከተሞች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት **105,926** ወይም ከጠቅላላ ሕዝቡ **13.51** በመቶ ሲሆን፣ ቀሪው ማለትም **678,419**ኙ (**86.49**%) የገጠር ነዋሪ ነው። በክልሉ ውስጥ በከተማም በገጠርም ያለው የቤተሰብ ወይም ጢስ ብዛት **174,445** ነው። ይህም በአማካኝ ባንድ ቤተሰብ ውስጥ **4.5** ሰዎች ሲኖሩ፣ ከዚህ ውስጥ በገጠር **4.7** ሰዎች፣ በከተማ **3.6** ባንድ ቤተሰብ ውስጥ ይገኛል።

**የቤንሻጉል-ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የሚኖሩ ነገዶች ሥብጥርና ብዛት ማሳያ ሠንጠረዥ(5)፤**

| ተራ ቁጥር | ነገዶች | ዘመን 1994 እኤአ | ዘመን 2007 እኤአ |
|---|---|---|---|
| 1 | በርታ | 27% | 25.41% |
| 2 | ዐሚራ | 22% | 21.69% |
| 3 | ጉሙዝ | 23% | 20.88% |
| 4 | ኦሮሞ | 13% | 13.55% |
| 5 | ሺናሻ | 7% | 7.73% |
| 6 | አገውአዊ | === | 4.22% |
| | | | |

እኤአ በ1994 በተደረገ ውቆጠራ የቤንሻጉል-ጉሙዝ ክልል ሕዝብ ቁጥር **460,459** እንደሆነ ተዘግቧል። ከዚህ ውስጥ **233,013** ወንዶች፣ **227,446** ሴቶች ናቸው። ከጠቅላላው ሕዝብ **36,027** የከተማነዋሪዎች ሲሆኑ፣ የቀረው**424,432** የገጠር ነዋሪ ነው።

የ2007 እኤአ ሚ ጃ መሠረት፣ ከቤንሻጉል-ጉምዝ ክልል ነዋሪ ውስጥ የንፁሕ ውኃ አቅርቦት የሚያገኘው **27.23** በመቶውብቻነ ው። ከዚህ ውስጥ **22.35** የከተማነ ዋሪዎች ሲሆኑ፣ **58.53**ቱ ገጠሬዎች ናቸው።

እንደ እኤአ 2005 ሚ ጃ ከሕዝቡ **19.1** ከመቶ የሚሆነ ውከድህነ ት ወለል በታች በሆነ የኑሮ አዘቅት ውስጥ የሚማስን ነው። ከሕዝቡ ማንበብና መጻፍ የሚችለው ወንዶች**47.4%፣** ሴቶች **23.2%** ናቸው። ከሚወለዱት ሕፃናት ከመቶ **84**ቱ ይሞታሉ። ይህምከአገሪቱ አጠቃላይ የሕፃናት ሞት ጋር ሲነፃጸር በ7 ይበልጣል።

ከሠንጠረዡ ለሚረዳት እንደሚቻለው፣ በቤንሻጉል-ጉሙዝ ክልል 6 ነገዶች ይገኛሉ። በሕገ መንግሥቱ ግን የክልሉ ባለቤት የቤንሻጉል-ጉሙዝ ሕዝብ እንደሆነ ይደነግጋል። በዓላማው ሥር ደግሞ፤ «የበርታ፣ የጉሙዝ፣ የሽናሻ፣ የማኦ እና የኮሞ ብሔረሰቦች እና ሌሎች በክልሉ የሚኖሩ ሕዝቦች» በማለት ለነዋሪዎቹ ዕውቅና ይሰጣል። ይህ ለትርጉም እና ለአፈጻጸም አስቸጋሪ ነው። ግልጽነት ይጎድለዋል። በዚህምየተነሳ የዐሚራውነገድ ተወላጆች በተደጋጋሚበክልሉ የሺናሻና የጉሙዝ ተወላጅ ባለሥልጣኖች በግፍና በገፍ ከማደላቸውም በላይ እንዲፈናቀሉ ተደርጓል። ሚ ጃው እንደሚያሣክተው ዐሚራው በቁጥሩ ከበርታ ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ነው ያለው። ይህ ሕዝብ በክልሉ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብት ፈጽሞ የለውም። ይህ እንኳ እንደቅንጦት ቢቆጠር፣ ሠርቶ የመኖር መብት የለውም። ከሁሉምበላይ በክልሉ ከሚገኙት ከተሞች ዐሚራውከፍተኛ ቁጥር እያለው፣ ተወካዮችን የመምረጥምሆነ የመመረጥመብት የለውም።

## 2.6 የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት፣

የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት በአዋጅውቁጥር 46/1994 ተሻሽሎእና በአቶ ሱፊያን አህመድ ተፈርሞየጸደቀውመግቢያ እንዲህ ይላል።

«እኛ የኦሮሞሕዝብ በእኛና በሌሎች የአገሪቱ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ላይ ተንሰራፍቶ የነበረው የጭቆና ሥርዓት ሰባዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን አፍኖ በተዘቡ ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች በመተብተብ ለድህነትና ለኋላ ቀርነት ዳርጎን በገዛ አገራችን እንደ ሁለተኛ ዜጋ በመቆጠር የሰቆቃ ኑሮ እንድናሳልፍ ሚድረጉን በመቃወምና በሚያዳግም ሁኔታ ማታረም እንዳለበት በማመን ሥርዓቱን ገርሥሠን የጣልን በመሆኑ፣

«ሥርዓቱ ከተገረሠሠ በኋላ በአገራችን የግለሰቦችና የማኅውብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ማንጠልን ጨምሮ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በሙሉ

የተከበሩበትና በአጠቃላይ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት የፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሥርዓት ማንባት የሚነጠንን ጠቀሜታ በማንዘብ ሕገ-መንግሥታችን በጋራ ያጸደቅን በመሆኑ፤ »

እነዚህን ዓላማዎች ማሳ በሚድረግ፣ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 8 **«የኦሮሞ ሕዝብ የክልሉ የበላይ ሥልጣን ባለቤት ሲሆን፣ የሕዝቡ የበላይነት ትምየማ ለጸውበሚሮጣቸውተወካዮቹና ራሱበቀጥታበሚያደርገውዲሞክራሲያዊ ተሳትፎነው።** » በማለት የሥልጣን ባለቤቱን በሚያሻማ መንገድ የኦሮሞ ሕዝብ እንደሆነ ያረጋግጣል። ከዚህ ላይ ብሔር፣ ብሔረሰቦች ሕዝቦች ብሎ ሜጩበር የለም። አንድ ሕዝብ፣ እርሱም ኦሮሞ ብቻ። ሌላው በዚያ ኦሮሚያ ተብሎ በታጠረ ክልል የሥልጣንምሆነ የባለቤትነት መብት የለውም።

እንደ አገሪቱ ማዕከላዊ ስታትስቲክ ማሥሪያ ቤት እኤአ የ2007 ሚ ጃ ሜሠረት፣ የኦሮሚያ ክልል የቆዳ ሥፋት **354,006.81** ስኩዌር ኪሎ ሜትር ነው። በአንድ ስኩዌር ኪሎ ሜትር ውስጥ የሚኖረውየሰዎች ብዛት **76.93** ነው። የሕዝቡ ብዛት **26,993,933** ነው። ከጠቅላላው የክልሉ ነዋሪ ውስጥ **13,595,006** ወንዶች ሲሆኑ፣ **13,398,927** ሴቶች ናቸው። ከዚህ ውስጥ በከተሞች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት **3,370,040** ወይም ከጠቅላላ ሕዝቡ **11.3%** ሲሆን፣ ቀሪው ማለትም **23,623,893**ቱ (**87.51**%) የገጠር ነዋሪ ነው። በክልሉ ውስጥ በከተማም በገጠርም ያለውየቤተሰብ ወይም ጠስ ብዛት **5,590,530** ነው። ይህም በአማካኝ ባንድ ቤተሰብ ውስጥ **4.8** ሰዎች ሲኖሩ፣ ከዚህ ውስጥ በከተማ**3.8** ባንድ ቤተሰብ ውስጥ ይገኛል።

እንደ ማዕከላላዊ ስታትስቲክ የ2004 እኤአ ሚ ጃ ሜሠረት፣ በኦሮሚያ ክልል ከሚኖረውየገጠር ነዋሪ ሕዝብ የንፁሕ ውኃ ተጠቃሚው ከሕዝቡ **32%ነው፤** ይህ በገጠር **23.7%** ብቻ ሲሆን፣ የከተማነዋሪው **91.03** @ነው።

በሌላ በኩል እንደ ማሥሪያ ቤቱ የ2005 እኤአ ሚ ጃ ሜሠረት፣ ከጠቅላላውየኦሮሚያ ክልል ነዋሪ ሕዝብ ውስጥ ከመቶ **19.9** የሚሆነ ውከድህነት ወለል በታች በሆነ አስከፊ የድህነት ኑሮ የሚኖር ነው። ከሕዝቡ ውስጥ ማንበብና ሜጻፍ የሚችለው ወንድ 61.5%፣ ሴት 29.5% መሆናቸውን ሚ ጃው ያሳያል። በሕፃናት ጤንነት ረገድ ከ1000 (ከሺ) **76** የሚሆኑት እንደተወለዱ ይሞታሉ። ይህምከአጠቃልይ የአገሪቱ በሺ **77** ከሆነ ውጋር ሲነፃጸር፣ የኦሮሞየ ሕፃናት ሞት፣ በሺ **1** እንደሚያንስ ያሳይል።

**በኦሮሞክልላዊ መንግሥት ክክል የሚኖሩ ነገዶች ሥብጥርና ብዛት ማሳያ ሠንጠረዥ(6)፤**

| **ተራ ቁጥር** | **ነገዶች** | **ዘመን 1994 እኤአ** | **ዘመን 2007 እኤአ** |
|---|---|---|---|
| 1 | ኦሮሞ | 85% | 87.81% |
| 2 | ዐማራ | 9.1% | 7.22% |
| 3 | ጉራጌ | 0.98% | 0,93% |
| 4 | ሌሎች | 4.6% | 4% |

ከሠንጠረዡ ለሚረዳት እንደሚቻለው፣ ኦሮሚያ በሚባለው ክልል በቁጥር ከፍተኛ ማከን ያላቸው 4 ነገዶች ይገኛሉ። ከነዚህ በተጩማሪ ከጠቅላላው ሕዝብ 4 በመቶ የሚሆኑ ሌሎች ነገዶች እንዳሉ ሚ ጃዎች ያሳያሉ። በሕገ መንግሥቱ ግን የክልሉ ባለቤት እና ባለሙሉ ሥልጣን ኦሮሞብቻነው። በዚህ ክክል ያሉት የዐማራ፣ የጉራጌና የሌሎች ነገድ አባሎች በክልሉ የመምረጥና የመመረጥ መብት የላቸውም። ባህልና ቋንቋቸውን የማጠቀምና የማዳበር መብት የሌላቸው ናቸው። በክልሉ የሚኖሩት በኦሮሞክልል ባለሥልጣኖች ሜልካም ፈቃድ ብቻ ነው። ሠፈውእና ለሙያገሪቱ ክፍል ለአንድ ነገድ ተሚርቆ ለኦሮሞፖለቲከኞች ገጸ በረከት ተሰጥቷል። ዐማራውእንደሌሎቹ ሁሉ ለዚህምክልል ባይተዋር ነው። በተቃራኒ ው የአማራ ክልል ለተባለው ክልል በተሰጠ ህገመንግስት ውስጥ ኦሮሞ የራሱ ዞን እንዲኖረውተደርጎ የፓርላማውክልናና የቋንቋ መማርና ማስተዳደር ስልጣን ተስጥቶታል።

**2.7 የሐረሪ ክልላዊ መንግሥት፣ ሕገ-መንግሥት፡-**

የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግሥት፣ ማከረም 30 ቀን 1997 ዓም ተሻሽሎ በፉአድ ኢብራሂም ተፈርሞ የፀደቀውሕገ-መንግሥት መግቢያ እንዲህ ይላል።

«እኛ የሐረሪ ሕዝብ ክልል ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሲደርስባቸውየነበረውን ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ባህላዊ ሃይማኖታዊ ጭቆና ጫና እና ተጽዕኖ በተለያየ ስልት ሜኪና ቦታ ሲታገሉ ቆይተውበሜኤሺ በግንቦት ወር 1983 ለዚህ ሁሉ ምክንያት የሆነ ውን ሥርዓት በሚያዳግም ሁኔታ ለማጣል በመቻሉ በተለይ ጭቁን ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር ታሪካቸው ባህላቸውና ቋንቋቸውን ለማዳበር በአጠቃላይ ብሔራዊ ኅልውናቸውን ለማጠበቅ የሚያስችላቸውን ምቹ ሁኔታ ሚፈጠሩንና ይህም ኅዳር 29 ቀን 1987 ዓም በኢትዮጵያ ሕዝቦች በፀደቀው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ሚረጋገጡን በማ ንዘብ፤

«የሐረሪ ሕዝብ ምንምእንኳን በምዕተ ዓሙታት ለሜቆጠር ዘመን ራሱን በራሱ ያስተዳደረ በራሱ ታሪክ ወግና ባህል ይኮራ የነበረ ቢሆንም በ1886 ዓም በተደረገ ውወረራ በነ ፍጠኛው ሥርዓት ሥር ከመውደቁምበላይ ይህን ሥርዓት ለማስወገድ በተለያዩ ጊዜያት ባደረገ ውንቅናቄና ትግል ምክንያት ለግርፋት፣ ለእስራትና ብሎምለስደት በመዳረጉ በራሱ ክልል በቁጥር አናሳ ሚሆኑ የተነ ሳ ልዩ አወካከል ስልት ማስፈለጉን በሚ ዳት፤

«የሐረሪ ሕዝብ ሲደርስበት የነበረውን ግፍና ጭቆና ሲካፈሉ ከነበሩት ከአካባቢው የኦሮሞ ሕዝብና ክልሎች የክልሉ ነዋሪ ሕዝቦች በመሆን የክልሉን አስተዳደር በጋራ ሚቋቋምና ማምራት ያለባቸውሚሆኑን በማጤን፣ »ወዘተ

እነዚህን በማሻ ዓላማ ት በማያዝ፣ የክልሉ ባለቤትነ ት ማን እንደሆነ በሕገ-መንግሥቱ **አንቀጽ 8 እንደሚከተለው ያስረዳል። «የሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነ ት የሐረሪ ሕዝብ የክልል የበላይ ሥልጣን ባለቤት ሲሆን፣ የሕዝቡ የበላይነ ትም የሚ ለጸው በዚህ ሕገ መንግሥት መሠረት በሚሮጣቸውተወካዮችና ራሱ በሚያደርገ ውዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነ ው።»**

እንደ አገሪቱ ማዕከላዊ ስታተስቲክ ማሥሪያ ቤት እኤአ የ2007 ሚ ጃ መሠረት፣ የሐረሪ ክልል የቆዳ ሥፋት **311.25** ስኩዌር ኪሎ ሜትር ነ ው። በአንድ ስኩዌር ኪሎ ሜትር ውስጥ የሚኖረውየሰዎች ብዛት **589.05** ነ ው። የጠቅላላው የሐረሪ ሕዝብ ብዛት **184,415** ነ ው። ከዚህ ውስጥ **92,316** ወንዶች ሲሆኑ፣ **91,099** ሴቶች ናቸው። ከዚህ ውስጥ በከተሞች የሚኖረውሕዝብ ብዛት **99,368** ወይም **54.18** ነ ው። በክልሉ ውስጥ በከተማም በገ ጠርም ያለው የቤተሰብ ወይም ጠስ ብዛት **46,169** ነ ው። ይህም በአማካኝ ባንድ ቤተሰብ ውስጥ **3.9** ሰዎች ሲኖሩ፣ ከዚህ ውስጥ በከተማ **3.4**፣ በገ ጠር **4.6** ባንድ ቤተሰብ ውስጥ ይገ ኛል።

እንደ ማዕከላዊ ስታተስቲክ የ2004 እኤአ ሚ ጃ መሠረት፣ በሐረሪ ክልል ከሚኖረው ሕዝብ **73.26** ሰዎች የንፁሕ ውኃ ተጠቃሚዎች ናቸው። ከዚህ ውስጥ **39.83 %** ቱ ገ ጠሬዎች ሲሆኑ፣ **95.28%** ከተሜዎች ናቸው።

በሌላ በኩል እንደ ማሥሪያ ቤቱ ከጠቅላላው የሐረሪ ክልል ነ ዋሪ ሕዝብ ውስጥ ከመቶ **5.7** የሚሆነ ው ከድህነ ት ወለል በታች በሆነ የድህነ ት ኑሮ የሚኖር ነ ው። ማንበብና ሚጻፍ ይችላል የተባለውከሕዝቡ **78.4** %ወንዶች፣ **54.9%** ሴቶች ሚሆናቸውን ሚ ጃውይጠቁሜል። በሕፃናት ጤንነ ት ረገ ድ ከ1000 (ከሺ) **66** የሚሆኑት እንደተወለዱ ይሞታሉ። ይህም ከአጠቃልይ የአገሪቱ በሺ 77 ከሆነ ው ጋር ሲነ ፃጸር፣ የሐረሪ የሕፃናት ሞት፣ በሺ 11 እንደሚያንስ ያሳይል።

**በሐረሪ ክልላዊ መንግሥት ክክል የሚኖሩ ነገዶች ሥብጥርና ብዛት ማሳያ ሠንጠረዥ(7) ፤**

| ተራ ቁጥር | ነገዶች | ዘመን 1994 እኤአ | ዘመን 2007 እኤአ |
|---|---|---|---|
| 1 | ኦሮሞ | 52.3% | 56.41% |
| 2 | ዐማራ | 32.6% | 22.77% |
| 3 | ሐረሪ | 7.1% | 8.65% |
| 4 | ጉራጌ | 3.2% | 4.34% |
| 5 | ሶማሊ | 1.68% | 3.87% |
| 6 | ትግሬ | 1.71% | 1.53% |
| 7 | አርጎባ | === | 1.26% |

ከሠንጠረዡ ለሚረዳት እንደሚቻለው፣ ሐረሪ በሚባለው ክልል በቁጥር ብዙኃኑን እንዳሻቸው እንዲያደርጉ የክልሉ ባለቤትነት ከተሰጣቸው ከኦሮሞውና ከዐማራው ከአምስትና ከ7 እጥፍ በላይ ለሚበልጧቸው ሁለት ነገዶች አሉ። የዲሞክራሲ አንዱ መርሕ የብዙዎች መብትና ፍላጎት ገዥ፣ የአናሳዎች መብትና ፍላጎት ተከባሪ የሚሆነው ሆኖ ተብሎ ተረግጦ፣ የአናሳዎቹን ፍላጎትና መብት በብዙኃኖቹ ላይ እንዲጫን ተደርጓል። የትግሬ-ወያኔ አገዛዝ ዘረኛ፣ ከፋፋይ፣ አገርና ትውልድ አጥፊ ነው የሚባለው ዝተብሎ አለመሆኑ ከዚህ በላይ ምን ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል። በዚህ ክልል ብዙኃኑ ኦሮሞዎችና ዐማሮች የጥቂቶቹ የሐረሪዎች ተገዥዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ መኖርና አየር መተንፈስ የሚችሉት በአናሳዎቹ ሐረሪዎች ፍላጎት ነው። በሕገ መንግሥቱ ግን የክልሉ ባለቤት እና ባለሙሉ ሥልጣን ሐረሪዎች ብቻ ናቸው።

**2.8 የትግራይ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት፡-**

የትግራይ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት የተጻፈው በእንግሊዝኛ ነው። የአማርኛ ቅጅ ለማግኘት አልተቻለም። ሚጃው የተጠናቀረው ከእንግሊዝኛው በመሆኑ የትርጉሙ ቀጥተኛ እንዳልሆን ግንዛቤ ይያዝ።

እኤአ ጁን 19/ 1995 በጸደቀው የትግራይ ክልላዊ መንግሥት ሕገ-መንግሥት መግቢያ ላይ እንዲህ ይላል፤

- የትግራይ ሕዝብ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ሕዝቦችና ብሔረሰቦች መካከል አንዱና በፊውዳል ሥርዓት የጣከራ ቀንበር ከተሸከሙት አንዱና ከ1975 እስከ 1991 ባለው ጊዜ ከጭቆና ነፃ ለመውጣት ከሌሎች ተጨቋኝ ኢትዮጵያውያን ወንድሞች ጋር በመተባበር የተራዘመ የትጥቅ ትግል በማድረግ ከ60 ሺ በላይ ሕይዎት እና ግዙፍ ቁሳቁስ ወድመት ያስከተለ ትግል ማድረጉ፤
- ከረጅም እና ደም አፋሳሽ ከሆነ ጦርነት በኋላ የትግራይ ሕዝብ ጨቋኙን አገዛዝ በማደምሰስ የሽግግር መንግሥት መመስረት መቻሉ እና፣ የትግራይ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለው መብቱ ያላንዳች ቅድመሁኔታ የተጠበቀ መሆኑን በማገንዘብ፣ ለዚህምእንዲረዳ ይህ ሕገ-መንግሥት መጽደቁን ይገልጻል።

እነዚህን በማሻ ዓላማት በማያዝ፣ የክልሉ ባለቤትነት ማን እንደሆነ በሕገ-መንግሥቱ **አንቀጽ 8 (1) እና (2) እንደሚከተለው ይላል። « የትግራይ ሕዝብ የትግራይ ክልላዊ መንግሥት የበላይ የሥልጣን ባለቤትነት ነው። የሕዝቡ የበላይ ሥልጣን ባለቤትነትም በቀጥታ በሚመርጣቸውተወካዮቹና በራሱ ቀጥተኛ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ነው» ይላል።**

ልክ ለሌሎቹ ክልሎች የማንጠልን መብት እንደፈቀደ ሁሉ፣ የሁሉም ነገር ፈጣሪው የትግሬ ወያኔ ቡድን ፣ ወያኔ በፈለገ ወቅት ልገንጠል ባለ ጊዜ ማንጠል የሚያስችለውን ሕግ ለራሱም ደንግጓል። የአገሪቱምሆነ የትግራይ ክልል ባለመብትና ባለሥልጣን የሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ እንደሆነ ለ28 ዓመታት የተጓዘባቸው መንገዶች ያስረዳሉ። እናም የትግራይ ክልል ባለመብት ትግሬ ብቻ ነው።

እንደ አገሪቱ ማዕከላዊ ስታትስቲክ ማሠሪያ ቤት እኤአ የ2007 ሚ ጃ መሠረት፣ የትግራይ ክልል የቆዳ ሥፋት **41,409.95** ስኩዌር ኪሎ ሜትር ነው። በአንድ ስኩዌር ኪሎ ሜትር ውስጥ የሚኖረውየሰዎች ብዛት **100** ነው። የጠቅላላውየትግራይ ሕዝብ ብዛት **4,316,988** ነው። ከዚህ ውስጥ **2,126,465** ወንዶች ሲሆኑ፣ **2,190,523** ሴቶች ናቸው። በከተሞች የሚኖረው ሕዝብ ብዛት **844,040** ወይም **19.55** ነው። በክልሉ ውስጥ በከተማም በገጠርም ያለው የቤተሰብ ወይም ጢስ ብዛት **992,635** ነው። ይህም በአማካኝ ባንድ ቤተሰብ ውስጥ **4.4** ሰዎች ሲኖሩ፣ ከዚህ ውስጥ በገጠር ባንድ ቤተሰብ ውስጥ **4.6** ሰዎች ይኖራሉ።

እንደ ማዕከላላዊ ስታትስቲክ የ2004 እኤአ ሚ ጃ መሠረት፣ በትግራይ ክልል ከሚኖረው ሕዝብ **53.99%** የንፁሕ ውኃ ተጠቃሚዎች ናቸው። ከዚህ ውስጥ ከመቶ **42.68**ቱ ገጠሬዎች ሲሆኑ፣ **97.28** ከተሞች ናቸው። ይህም ከሌሎች ክልሎች ጋር ሲነፃፀር፣ የክልሉ ሕዝብ የንፁሕ ውኃ ተጠቃሚ ቱ ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል።

በሌላ በኩል እንደ ማሠሪያ ቤቱ የ2005 ሚ ጃ መሠረት ከጠቅላላው የትግራይ ክልል ነዋሪ ሕዝብ ውስጥ ከመቶ **31.6** የሚሆነ ው በድህነት ወለል በሆነ ኑሮ የሚኖር ነው። ማንበብ እና መጻፍ የሚችለው **67.5**% ወንዶች፣ **33.9%** ሴቶች መሆናቸውን ሚ ጃው ይጠቁማል። በሕፃናት ጤንነት ረገድ ከ1000 (ከሺ) **67** የሚሆኑት እንደተወለዱ ይሞታሉ። ይህም ከአጠቃልይ የአገሪቱ በሺ 77 ከሆነው ጋር ሲነፃጸር፣ የትግራይ የሕፃናት ሞት፣ በሺ 10 እንደሚያንስ ያሳይል። ይህም የክልሉን ሕዝብ ከሚይምት ለማላቀቅ፣ ጤንነቱን ለማጠበቅና የዘመናዊ ሕይዎት እንዲመራ ለማስቻል ፣ ባለፉት 28 ዓመታት አድላዊ በሆነ የበጀት ድልድና ዘረፋ ምን ያህል እርቀት እንደተጓዙ ያሳያል።

**በትግራይ ክልላዊ መንግሥት ክክል የሚኖሩ ነገዶች ሥብጥርና ብዛት ማሳያ ሠንጠረዥ(8) ፤**

| **ተራ ቁጥር** | **ነገዶች** | **ዘመን 1994 እኤአ** | **ዘመን 2007 እኤአ** |
|---|---|---|---|
| 1 | ትግሬ/ተጋሩ | 94.98% | 96.55% |
| 2 | ዐማራ | 2.6% | 1.63% |
| 3 | ኢሮፕ | 0.7% | 0.71% |
| 4 | አፋር | == | 0.29% |
| 5 | አገው | == | 0.17% |
| 6 | ኦሮሞ | === | 1.53% |
| 7 | ኩናማ | 0.05% | 0.07% |

ከሠንጠረዡ ለሚረዳት እንደሚቻለው፣ የ1994ቱ ከ2007 ቱ ሲነፃፀር፣ በክልሉ የሚኖሩት ነገዶች ሁሉም የተወሰነ ጭማሪ ሲያሳዩ፣ የዐማራው ሕዝብ በ1994 ከነበረው 2.6% በ2007 በ0.9% ቀንሷል። ለምን? ይኸም ሆኖ፣ ከአጠቃላይ ነዋሪው ከ5% በላይ የሕዝብ ብዛት ያላቸው 6ቱ ነገድና ጎሣዎች በክልሉ መብትና ሥልጣን የላቸውም።

**2.9 የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልል ማግሥት ሕገ-መንግሥት፤**

**የክልሉ መንግሥት ሕገ-መንግሥት በመግቢያው ላይ እንዲህ ይላል፡-**

*«እኛ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፤ በጋራ በሚቃቀድና በዕኩልነት ላይ ተመሥርተን በቋቋምነው ክልላችን የሕግ የበላይነት፣ እንዲሰፍን፣ ኢኮኖሚ ማኅበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን፣ የራሳችን ዕድል በራስ የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ ቋንቋችን ባህላችንና አንድነታችን ይበልጥ ለማጠናከር፣ ማንነታችን ተከብሮ በትግላችንና በከፈልነው መስዋዕትነት የተገኘውን ዲሞክራሲና ሰላምአላቂነት ለሚያጋገጥ፤*

*«በክልላችን ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የግለሰብ፣ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ማክበራቸውን፣ የፆታ ዕኩልነት ሚያጋገጡን፤ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች ያላንዳች ልዩነት በዕኩልነት እንዲራመዱ ጽኑ እምነታችን በመሆኑ፤*

*«የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የራሳችን የሆነ አኩሪ ባህልና ፣ የራሳችን መልክዐ-ምድራዊ አሠፋፈር ያለን፣ በተለያዩ መልኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረን አብረን የምንኖርበት ክልላችን በመሆኗ፣ ያፈራነው የጋራ ጥቅምና አማካከት አለን ብለን ስለምናምን፣ ቀጣዩ የጋራ ዕድገታችን መመሥረት ያለበት ካለፈው ጨቋኝ ሥርዓት የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በሚያምና የጋራ ጥቅማችንን በማጎደግ ላይ ሚሆን ስላለበት፤»ወዘተ በማለት ከስምንቱ ክልሎች ባፈነፈጠና የግለሰብን ነፃነት ባወቀ መልኩ ዓላማውን ገልጿል። ይህ ክልል ከሌሎቹ የክልል ሕገ-መንግሥቶች በተለየ መልኩ ዓላማውን መግለጹ ምናልባች በአማካከት ኢትዮጵያዊነት ያማዛነባቸውሰዎች፣ ወይምበክልሉ የአንድምነገድ በቁጥር ከሌሎች ጋር ሲነፃፀር ጎልቶ ያለመውጣት የአቻነት ስሜት መልበት፣ ወይምነገን አሻግረው የሚማከቱ ሰዎች በሕግ አዘገጃጀቱ ውስጥ ከፍተኛ ሚና መጫዎት ወዘተ ሕጉ ዐሚራውንና ያለፉትን ሥርዓቶች በድፍኑ ከማውገዝ መቆጠቡ ይስተዋላል።*

ከላይ በተጠቀሱት የመግቢያውዓላማዎች መሠረትነት፣ የሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 8(1) «የደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የክልሉ መመንግሥት የበላይ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው»ይላል። ሕገ-መንግሥቱ በመግቢያው የግለሰቦችን መብትና ነፃነት የተቀበለ ይሁን እንጂ፣ በተግባር ግለሰቦች መብትምሆነ ነፃነት የላቸውም፡ ከሁሉምበላይ በክልሉ ከሚኖሩት ነገዶች አንዱ የሆነው፣ በግለሰብምሆነ በቡድን በክልሉ ውስጥ ዲሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ቀርቶ፣ በክልሉ የመኖር የዜግነት መብት የለውም፡ አቶ ሽ,ፈታራውሽጉጤ የክልሉ ርዕሰ ማስተዳደር በነበረበት ከ2002 እስከ 2005 ባሉት ዓመታት ብቻ ከመቶ ሺዎች በላይ ዐማራዎችን በክልሉ የመኖር መብት የላችሁም ብሎ በገፍ የሚያ ድለውን አገድሎ ሌሎቹን ንብረታችን በማዘረፍ አፈናቅሏቸዋል። ይህም ሕገመንግሥት ተብየው ለብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሰጡሁት ያለውመብትና ነፃነት ከወረቀት ያለፈ አለሚሆኑ ማሳያ ነው።

እንደ አገሪቱ ማዕከላዊ ስታተስቲክ ማሠሪያ ቤት እኤአ የ2007 ሚረጃ መሠረት፣ የደ/ብ/ብ/ሕ ክልል የቆዳ ሥፋት **105,887.18** ስኩዬር ኪሎሜትር ነው። በአንድ ስኩዬር ኪሎሜትር ውስጥ የሚኖረውየ ሰዎች ብዛት **141** ነው። የጠቅላላውየደብብሕ ክልል ሕዝብ ብዛት **14,929,548** ነው። ከዚህ ውስጥ **7,425,918** ወንዶች ሲሆኑ፣ **7,503,630** ሴቶች ናቸው። ከዚህ ውስጥ በገጠር የሚኖረውሕዝብ ብዛት **13,433,991** ወይም **89.98%** ሲሆን በከተማየ ሚኖረውደግሞ **1,495,557** ወይም **10.02%**። በክልሉ ውስጥ በከተማምበገጠርም ያለውየቤተሰብ ወይምጢስ ብዛት **3,110,995** ነው። ይህም በአማካኝ ባንድ ቤተሰብ ውስጥ **4.8** ሰዎች ሲኖሩ፣ ከዚህ ውስጥ በከተማ**3.9**፣ በገጠር **4.9** ባንድ ቤተሰብ ውስጥ ይገኛል።

እንደ ማዕከላላዊ ስታተስቲክ የ2006 እኤአ ሚረጃ መሠረት፣ የደብብሕ ክልል ከሚኖረውሕዝብ **54%** የንፁሕ ውኃ ተጠቃሚዎች ናቸው። ከዚህ ውስጥ **39.83 %**ቱ ገጠሬዎች ሲሆኑ፣ **95.28%** ከተሜዎች ናቸው።

በሌላ በኩል እንደ ማሠሪያ ቤቱ የ2005 ሚረጃ ከጠቅላላውየደብብሕ ክልል ነዋሪ ሕዝብ ውስጥ **10.7 %** የሚሆነው ከድህነት ወለል በታች በሆነ የድህነት ኑሮ የሚኖር ነው። ማንበብና መጻፍ ይችላል የተባለው **ከሕዝቡ** 57 %ወንዶች፣ **22.4%** ሴቶች መሆናቸውን ሚረጃው ይጠቁማል። በሕፃናት ጤንነት

ረገድ ከ1000 (ከሺ) **85** የሚሆኑት እንደተወለዱ ይሞታሉ። ይህም ከአጠቃልይ የአገሪቱ በሺ 77 ከሆነው ጋር ሲነፃጸር፣ የሐረሪ የሕፃናት ሞት፣ በሺ 8 እንደሚበልጥ ያሳይል።

**በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ክክል የሚኖሩ ነገዶች ሥብጥርና ብዛት ማሳያ ሠንጠረዥ(9) ፤**

| **ተራ ቁጥር** | **ነገዶች** | **ዘመን 1994 እኤአ** | **ዘመን 2007 እኤአ** |
|---|---|---|---|
| 1 | ሲዳማ | 18% | 19.38% |
| 2 | ወላይታ | 12% | 10.59% |
| 3 | ሐዲያ | == | 7.98% |
| 4 | ጉራጌ | 15% | 7.54% |
| 5 | ጋሞ | == | 7% |
| 6 | ከፍቾ | == | 5.44% |
| 7 | ዐማራ | === | 4.10% |
| 8 | ሌሎች | ==== | 37.97% የሚወክሉ ከ40 ያላነሱ ነገዶች አሉ |

ከሠንጠረዡ ሚረዳት እንደሚቻለው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክክል በቁጥሩ ከሌሎች ገዝፎ የወጣ ነገድ የለም። ባለሞኖሩም ምክንያት ይመስላል የክልሉ ማጡሪያ የተፈጥሮ አቀጣጫን ማመላከቻና ከኢትዮጵያ ደቡብ ያለ ሚሆኑን በሚያሳይ ሚልኩ እንዲጡራና የጥቅሉን የነገዶች ማጡሪያ እንዲዝ የተደረገው። ዐማራው ይህም ሆኖ፣ ከክልሉ ከፍተኛ ቁጥር አላቸው ከተባሉት ነገዶች በ7ኛ ደረጃ የሚገኝ ነው። በቀሩት 8 ክልሎች በቁጥሩ በሁለተኛ ደረጃ የሚገኝ ነው። ይህም ከሌሎች ነገዶች በአገሪቱ በሥፋት የተሠራጨብቻ ሳይሆን፣ የአገሪቱ ጥንታዊ ነገድ ከሆኑት አንዱና ዋናው ሚሆኑን ተጨባጭ ማሳያ ነው። ይህን ሕዝብ ነው በዘመን ወያኔ በሰው ሠራሽ ሕግ አገር አልባ እንዲሆን የተደረገው። የዐማራው ልጅ በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ አገሩን የተነጠቀ ሚሆኑን አውቆ፣ የአገሩን ባለቤትነት ሚልሶ ለመቀዳጀትና ኅልውናውን ለማስቀጠል በሁለንተናዊ ሚልኩ ዝግጁ ሚሆን ይጠበቅበታል። ዛሬ ለዐማራው የቀረው አንድና አንድ ብቻ ነው ። ተደራጅቶ የተነጠቀ ግዛቱን ማስመለስ። ይህ ተግባራዊ የሚሆነው ደግም በአንድና በአንድ መንገድ ብቻ ነው። ይህንን ዐማራን ለማጥፋና ኢትዮጵያን ለማጥተን ተብሎ በሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ-ኦነግ ተግባራዊ የሆነን ሕገ-መንግሥት በመሻር ይሆናል። ከዚህ በመለስ ዛሬ በኦነግና በኦዴድ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ የሚምራ የጥገና አካሄድ የዐማራን ኅልውና አይታደግም። የኢትዮጵያንም አንድነት አያስጠብቅም። ለሚድረግ የተነሳው ለወንጀለኛው ወያኔና ለተባባሪ ባንዶች ምሕረትን፣ ለኢሕአዴግ የመቀባበት ለውጥን በሚድረግ የተለመደ የሚጭበርበር ምርጫ ተብዬን በማካሄድ ያለውን የዘረኛና የጥፋት ሕገመንግሥት ይዞ ለመቀጠል ነው። የዐማራውን ዕልቂት ለማስቀጠል ነው። ከአባቱ ግዛት እንደተለየ የነሱ ሎሌ ሁኖ ማገራውን እንዲገፋ ለሚድረግ ነው። ይህንን ዐማራ አይቀበልም። በትግሉ ያጥፈዋል። ትግሉ ረጅም፣ መራር ሚሆኑን እንገነዘባለን። ድሉ ግን የዐማራና የኢትዮጵያ ሚሆኑን አንጠራጠርም።

***የክልሎች ስፋት በስኩዬር ኪሎሜትር፣ የሕዝብ ብዛት፣ በክልሎች የሚኖሩ ነገዶች ብዛት፣ እንዲሁምየ መሠረታዊ የኑሮ ደረጃ ማሳያ ሠንጠረዥ፤***

| | (1)ዐማራ | (2)አፋር | (3)ሶማሊ | (4)ጋምቤላ | (5)ቤንሻጉል-ጉሙዝ | (6)ኦሮሚያ | (7)ትግራይ | (8)ሐረሪ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቆዳ ሥፋት በስኩየር ኪሎሜትር | 157,708.96 | 96,707 | 279,254 | 29,788.22 | 49,289.98 | 353,006.81 | 41,409.95 | 311.25 |
| የሕዝብ ብዛት | 17,221,976 | 1,390,273 | 4,445,219 | 307,096 | 784,345 | 26,993,933 | 4,316988 | 184,415 |
| በስኩየር ኪ የነዋሪ ብዛት | 108.2 | 14.38 | 15.9 | 10 | 15.91 | 76.93 | 100 | 589.05 |
| የወንድ ብዛት | 8,641,580 | 175,117 | 2,472,490 | 159,787 | 398,655 | 13,595,006 | 2,126,465 | 92,316 |
| የሴቶች ብዛት | 8,580,396 | 615,156 | 1,972,729 | 147,309 | 385,690 | 13,398,927 | 2,190,523 | 91,099 |
| የከተማ ነዋሪ ብዛት | 2,112,595 | 185,135 | 623,004 | 77,925 | 105,926 | 3,370,040 | 844,040 | 99,368 |
| የገጠር ነዋሪ ብዛት | 15,109,381 | 409,123 | 1,687,986 | 2,29,171 | 678,419 | 23,623,893 | 3,432,948 | 85,047 |
| የቤተሰብ/ጤስ/ብዛት | 3,983,786 | 247,255 | 687,986 | 66,467 | 174,445 | 5,593,530 | 992,635 | 46,169 |
| የአማካኝ የአንድ ቤተሰብ ብዛት | 4.3 | | 6.8 | 4.6 | 4.5 | 4.8 | 4.4 | 3.9 |
| • በከተማ | -- | 5.6 | - | 3.8 | 3.6 | 3.8 | -- | 3.4 |
| • በገጠር | -- | 6 | - | 4.9 | 4.7 | 5.0 | 4.6 | 4.6 |
| ከነዋሪው የንፁሕ ውኃ ተጠቃሚው | 19.89% | 48.57% | 38.9% | -- | 27.23% | 32% | 53.99% | 73.26% |
| • ከተማ | 91.8% | 78.11% | 77.21% | | 58.53% | 91.04% | 97.28% | 39.83% |
| • ገጠር | - | 26.89% | 21.32% | | 22.35% | 23.7% | 42.68% | 95.25% |
| ከድህነት ወለል በታች ነዋሪ ብዛት | 17.5% (3,o13,845.8) | 67.3% (935,653.72) | 71.8% (3,191,667.242) | 44% (135,122.24) | 19.1% (149,809.895) | 19.9% (5,371,792.667) | 31.6% | 5.7% (10,511.655) |
| ማንበብና መጻፍ የሚችሉ | | | | | | | | |
| • ወንድ | 54% | 27% | 22% | 57.5% | 47.4% | 61.5% | 67.5% | 78.4% |
| • ሴት | 25.1% | 15.6% | 9.8% | 22.8% | 23.2% | 29.5% | 33,7% | 54.9% |
| የሕፃናት ሞት በሺ | 94 | 61 | 57 | 92 | 84 | 76 | 67 | 66 |
| በክልሎቹ የሚኖሩ ነገዶች | 6 | 7 | 7 | >10 | 6 | >4 | 7 | 7 |

| | |
|---|---|
| | ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች |

| | |
|---|---|
| የቆዳ ሥፋት በስኩየር ኪሎሜትር | 105,887.18 |
| የሕዝብ ብዛት | 14,929,548 |
| በስኩየር ኪ የነዋሪ ብዛት | 141 |
| የወንድ ብዛት | 7,425,918 |
| የሴቶች ብዛት | 7,503,630 |
| የከተማነዋሪ ብዛት | 1,495,557 |
| የገጠር ነዋሪ ብዛት | 13,433,991 |
| የቤተሰብ/ጢስ/ብዛት | 3,110,995 |
| የአማካኝ የአንድ ቤተሰብ ብዛት<br>• በከተማ<br>• በገጠር | 4.8<br>3.9<br>4.9 |
| ከነዋሪው የንፁሕ ውኃ ተጠቃሚው<br>• ከተማ<br>• ገጠር | 54%<br>39.83%<br>95.28 |
| ከድህነት ወለል በታች ነዋሪ ብዛት | 10.7% |
| ማንበብና መጻፍ የሚችሉ<br>• ወንድ<br>• ሴት | <br>57%<br>22.4% |
| የሕፃናት ሞት በሺ | 85 |
| በክልሉ የሚኖሩ ነገዶች | >50 |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |